# “ሕልምና ቅዥት” ክፍል ፩. የጐንቻው!

ከመስቀል ክብረ-በዓል ማግስት፤ከነገ ወዲያ የሚከፈተው የትምህርት ቤታችን ዕለት የእትየለሌ ያህል ተለጥጦ ራቀኝ። በተለይ ሌሊቱ ከቀኑ ሁለት እጅ ያህል ይከነዳል። በደስታና በጉጉት እያፍነከነከ በሚያቃትት ስሜት ከጠባብ አልጋዬ ተከስሜ በሃሳብ እየተናጥኩ፤ነገን እጅግ አድርጌ ናፈቅሁ። የዛሬን አዳር እንደ ጨርቅ ሳስታ የላመች አሮጊት የቆዳ ምንጣፌን (አጐዛዬን) በጀርባየና በፊቴ እየተገላበጥሁ እንደ እድሯ አለፋታለሁ፤ ሁለት እጆቼና እግሮቼ ወዝና ጢስ የጠገበች አንዷት ‘ቢቆጨኝ’ ብርድ ልብሴን እንዳኀበር ወጥረው አካሌን እንደ ሸማኔ እቃ ከአንጓ አንጓ ተሳስበው በሚደወሩ የሃሳብ መንጋዎች፤ የናፍቆትና የደስታ ስቃይ ጋር ወጥረው እያስቃተቱኝ ኀኔ የስንዝር ግማሽ አንሳፍፈፌ፤ አይኖቸ እንዳፈጠጡ እነሆ ሌሊቱ ተገባደደ።

አዚህ ዘመን ላይ ሆኜ ወዳ ኋላ በማጠንጠን ሳስበው እንዴት ደግ ዘመን ኖሯል? እንዲያ ነገን ለማየት በደስታ አስጨንቆ የሚጓጓ፤ተስፋ ሰጭ የጊዜና የቀን ሙሉ፤ እንዲህ ዛሬ በጎደሎው ዘመን ነገ የሚያመጣውን ከዛሬ የከፋ፤የከበደ ቀንን በመፍራት ስንቶች ሌሊቱ እንዲረዝምላቸው አልጋቸውን ሙጥኝ እንዳሉ፤ጉልበታቸውን እንደታቀፉ አሸልበው ይቆዩ ዘንድ ለጨለማው አማልክት በህልማቸው ይማፀናሉ፤ ለባለቀኖች ነግቶ አስላልፎ እንዳይሰጣቸው የነገን የቅዥት እውነታ በመስጋት፡፡

በዚያ የጐልማሳነት ዘመኔ፤ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤታችን በሰኔ ወር መጨረሻ ተዘግቶ ከደመራ በዓል ማግስት ተከፍቶ አዲሱ 8ኛ ክፍላችን እስክንገናኝ ድረስ ለሁለት ወር በላይ በመዘጋቱ ከጓደኞቻችና ከአስተማሪዎቻችንም ጋር በመለያየታችን ናፍቆት እንቅልፍ ነስቶኛል። ሁላችንም በየፊናችን ከተበታተንበት ሳልስት ጀምሮ የልጅነት ናፍቆት ቀን በሰመመን ሌሊት በሕልም ያሳስበናል፡፤ በዚያ ጊዜ ‘ሞባይል ስልክ’፤ ‘ኢሜል’፣ ‘ፌስቡክ’ ስላልተፈለሰሙ መገናኛችን በአካልና በዓይነ-ስጋ አልፎ አልፎም ‘በህልም’ ብቻ ነበር።

አስተማሪዎቻችንም ከመላው ኢትዮጵያ፤ እንደ ‘ድሮው አባባል’ ከ14ቱ ክ/ሀገራት የተውጣጡ ነበሩ፤ስለሆነም አብዣኞቹ በእረፍት ወራት ወደ ትውልድ ቀያቸው ሲመለሱ፤ሌሎቹ ደግሞ ለክረምት የሙያ ማሻሻያ ‘ኮርስ’ ይሄዳሉ። ዛሬ እንዲህ በዞን ቀመር ከፋፍለው፤ አራርቀው፤ አደናቁረው ሊገዙን።

አብዛኛው የገጠር ተማሪዎች ወደ ወላጆቻቸው ሄደው ድፍን ሁለት ወሩን የሚያሳልፉት በሥራ ተጠምደው ነው አንዳንድ ከተሜዎችም ወደ ገጠር ዘመድ ጥየቃ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ይሄዳሉ። እንግዳ ተቀባዩ የአገሬ ሕዝብ በደለበ ሙክትና ከዚያም በላይ አርዶ፤ደግሶ አስደስቶ የሚሸኝ ክቡር፤ኩሩ፤ባለጸጋና ጉዛም ነበር። ቤት ያፈራውን ብርቅዬ ቋጥሮ ይሸኝ እንደነበር አስታውሳለሁ የዛሬውን አያድረገውና እንዲህ ኑሮው፤አካሉና፤ ስብዕናው፤ኮስሶ፤ተጎሳቅሎ፤የባዕድ ተመጽዋች ሊሆን።

ዛሬ ንጋት አጥቢያ ላይ ውስጤን በስሜት ኮልኩሎ ብቻዬን እንደ እብድ ያሳቀኝን የልጅነት ሚስጥርና የትዝታ ስንክሳር በትንሹ ላውሳ። ከሁሉም በላይ በጣም ዳጎስ ብሎ የሚይታየኝ (የሚንገጣወርብኝ) የጓደኛችን የ‘**ደጉ**’ ትዝታ ነው።

**ደጉ፡** የምንለው ጓደኛችን ዋና ስሙ ለጊዜው ረሳሁት፤ በክፍላችን ካሉ እድሜ ጠገብ የገጠር ተማሪዎች አንዱ ነው፤ የሚኖረው፤ በደጋማው አምባ ምድር መገባደጃና በቆላ ምድር መዳረሻ ድንበር ላይ በምትገኝ አንድ የገበሬ መንደር ሲሆን በሙቀትም በብርድም የተፈተነ ታታሪ ጎረምሳ ነው። በሳምንት ሁለትና ሶስት ጊዜ ወደ ወላጆቹ መንደር እየተመላለሰ ስንቁን ይዞ ይመጣል።

**ደጉ**፤ በቁመናውና በተክለሰውነቱ ከአስተማሪዎቻችን አይተናነስም፤ ነገር ግን ቅንና ገራገር ስለሆነ በቀልድና ጨዋታ ሁሉም ይዳፈረዋል። ሲስቅም፤ጥርሱ ብቻ ሳይሆን ፊቱ ሁሉ ይፈካል፤ታዲያ ከትከት ብሎ ስቆ አያውቅም፤ ቢበዛ ጎርነን ካለ ድምጹ ጋር ከሳንባው አፈትልኮ ከሚጎሰም አንድ ቅኝት/ምት የትንፋሽ ‘እህ’ታ በስተቀር።

ከእድሜው ይልቅ፤የጀንሆይን ክቡር ዘበኛ የሚያስመስለው ልብሱና አለባበሱ ነው፤ ኮቱ ከካፓርት አይተናነስም፤ቀጥ ብሎ ሲቆም ቁምጣውን ይሰለቅጣታል። የኰቱ ኪሶች፤ከብብቱ ስር ጀምረው ወደ ጀርባና ፊቱም እያዋሰኑ እስከ ጉልበቱ አካለው በሰምበር ይወርዳሉ። የኮቱ ኪሶች የልጅ ቃጭል በሚያክል ቁልፍ አፋቸውን ተሸብበው፤ እንደ ጣሊያን የጥይት ሳጥንይገጠማሉ። ይሁንና የደጉ ኪሶች በረከት የተሞሉ የምሳ አገልግሎቻችን በመሆን ለክፍላችን ተማሪዎች ኃብሰተ-መና ቋጥረው የሚቸሩ፤ረድዔታም፤ቋቶች ናቸው። በነዚህ ኪሶች ሚስጥርና ውለታ የተነሳ ዋናውን ስሙን የሚያስንቅ ስም አውጥተን ‘**ደጉ**’ በማለት እያቆላመጥን እንጠራዋለን።

የኮቱ የቀኝ ኪሱ ከኪሎ በላይ የሚመዝኑ የገብስ፤የስንዴና የሽምብራ ቆሎ ተልይቷቸው አያውቅም ፤ የግራ ኪሱ ደግሞ ቢወረውሩት አናት የሚፈነክት ጠጣር ዳቦ ቆሎ መቋጠሪያ ነው።

**ደጉ** በክፍላችን መካከለኛ ረድፍ ወደ ኋላ አካባቢ ይቀመጣል፤ በተለይ በመጨረሻው ክፍለ ጊዜ በድካምና በሃሳብ ጭምር ስናዛጋ በርሃብ ስናፏሽግ ተጠቋቁመን የደጉን ኪስ በምልክት እንኳኳለን፤ደጉም ትንሽ ግጢጥ ካለ በኋላ ቀናው ጓደኛችን በእጁ እየዘገነ በወንበር ስርና አሻገር በሚቀባበሉ ቀልጣፋ እጆች ያድለናል፤ለገዳም መነኩሴና መናኝ በእፉኝ ተቀንኖ እንደሚቆረጥ የዕለት ቀለብ፤የፆም መፍቻ እየሰፈረ ይናኝናል፤በእርግጥም የረዴት ዘመን ነበርና እፍኝ ያጠግበን ነበር።

ይህንን የተቀነባበር እደላ በክፍል ውስጥ ያለው ተማሪ ሁሉ ደርሶት እስኪጠናቀቅ ከፊት ለፊታችን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ነጭ ኖራ እየከሰከሰ የሚጥፈው አስተማሪ አንድም ቀን ህውከት ፈጥሮ አያውቅም እንዲያውም ከንግግሩ ጋር ዙሪያ ገባውን በለሆሳስ ቆሎ ከሚያመነዝከው ጋር የሚፈጥረው የሚጥም ዑደት እንጅ። በዚያ ጊዜ ክፍል ውስጥ መብላት ነውርና የሚያስቀጣም ይመስለኛል።

ታዲያ በዚህ ‘ደገ/ገደ ቢስ’ ዘመን ጥቂት ደጉን የመሳሰሉ ተማሪዎችና ቤተሰቦች አልፎ፤አልፎ ቢኖሩ ኖሮ ባሁኑ ጊዜ በየትምህርት ቤቶች ጠኔ በየክፉሉ ለሚጥላቸው ተማሪዎች መድህን በሆኑ ነበር።

ደጉ፤ በጣም ለሚያቀርባቸው ጥቂት ተማሪዎች፤ የዳቦቆሎ እየዘገነ ይቸር ነበር እኔም ከነዚህ በቅርብ ከሚቀመጡ አንዱ ነበርኩ፡ ታዲያ ዳቦቆሎውን መቆርጠም ጥበብ ይጠይቃል። አንድ ጊዜ ትዝ ይለኛል፤ደጉ በእለቱ ወደ መንደሩ ይመለስ ስለነበር ከእረፍት መልስ በር ላይ ቆሞ ኪሱ እስኪራቆት ዳቦ ቆሎውን ለሁላችን አድሎ ከመጨረሱ ሕንዳዊው የባይዎሎጅ አስታማሪያችን እግር በእግራችን ተከታትሎን ገባ።

‘ሚስተር ሲንግ’ ፊቱን ወደ እኛ ሲያዞር የአፍ ኰቴያችን ጸጥ-ረጭ ይላል፤ወደ ጥቁር ሰሌዳው ሲዞር በቅጽበት ጥርድም-ድም፤እያለ አጥንት እንዲሚሰብር ውሻና አንዳንዱ ደግሞ የሚያንቀራጭጭው ድምጽ ምን ያሕል እንደሰቀጠጠው፤እንዳስደነገጠው፤ አሁንም ፊቱ ገርጥቶ ይታየኛል፤ ‘*ዎት ኢዝ ጎይንግ ኦን?*’ ካለ በኋላ መልስ ሲያጣ እኒህ አበሾች ጥሬ ስጋ ይወዳሉ ይባላል፤ብሎ በህሊናው ስንቅር ያለበትን አስፈሪ ሃሳብ እሱና ፈጣሪው ናቸው የሚያውቁት። ብቻ አኩርፎ ይሁን ደንግጦ ክፍሉን ተመናጭቆ ቦርሳውን ይዞ በፍጥነት ወጣ። በተፈጠረው ክፍተት የሚችለው ደቋቁሶ፤ያልሆነለት ያራሳትን አባብሶ ወደ ኪሱ አዛውሮ እንዳበቃ፤ የክፍል ዓለቃችን ተከታትሎት ወጣና የአበሻ መላ ፈልጎ፤ ይቅርታም ተጠይቆት ተመልሶ ገባ።

ታዲያ ከዚህ ዕለት በኋላ የደጉ ዳቦ ቆሎ በጥርስ አፈጫጨት ረቀቅ ያለ ሆነ፡፤ ሶስትና አራት በአንዴ ከጐረስን አይጥ እንደዋጠ እባብ በአለንበት አቀስሰን ከጉንጫችን ግድግዳዎች ከዳቦ ቆሎው ጋር በተዋሃዱ ቅመሞች፤ጨውና በርበሬ ማዕዛ ቆልምጠው በሚያመነጩት የምራቅ ፈሳሾች በምላስ አዘዋውረን በማዳረስ ጊዜ የሚፈጅ የማቅለጥና የሟሟት፤ጥበብን፤ትዕግስትን  የሚጠይቅ አዝጋሚ ተግባር ነበር።

አንዳንዴ ጣዕም ባይኖረው ኖሮ ጥንካሬው ጠጠር የቃሙ ይመስላል። አልፎ አልፎም ያልተፈለጉ ክስተቶች ያጋጥሙ ነበር፤ ለምሳሌ፤ ትንታ አናጥቧቸው በትናጋ ምላጭ ባርቀው፤ከአፍ አፈትልከው በመደዳ የተተኰሱና ዒላማቸውን የሳቱ አጋጣሚዎች ክፍላችንን በሣቅ ማዕበል ያናወጡበት ገጠመኞችን አስታውሳለሁ።

ዛሬ እዚህ ባለሁበት ‘ውጭ አገር’ የተማሪዎችን ቦርሳና ሻንጣ ግማሹን ቦታ አጣቦ የሚይዘው በየዕለቱ የሚሰንቁት ምግብና መጠጥ ሲሆን እንዳሻቸው አውጥተው ቢኮመኩሙ የሚጠይቃቸው የለም፡ ታዲያ ንፉግ ናቸው ወይም ይሉኝታ አያውቁም መሰል መ/ማካፈል ግን አያውቁም።

ይቅርታ! ሳላስበው የልጅነትና የጐልማሳነት የቆሎ ጓደኛየ ትዝታ ወደ ኋላ እንደዚህ እያንደረደረ በሃሳብና በጊዜ አዚህ ድረስ እንደውሃ ሙላት ይዞኝ ጭልጥ አለ።

ለነገሩ፤ ሳስባቸው ጥርስ የሚያበላልጡ ትዝታዎቸ ብዙ ናቸው፤ እንዲያው በትንሹ ልቆንጥር ብል እንኳ  ብዙ ተያያዥ ዶሴዎች ሊያስቃኙኝ ነው። እንዳሁኑ ዘመን ጎረምሳዎች እና ኰረዳዎች ፍቅር፤ሚስጥራችን ሁሉ በአደባባይ ባይሆንም የተባዕታይ አንስታይ ፆታዎች መካከል የነበረው ሽሙጥ፤አሉባልታ፤መስተፋቅር ዜና ቀልብን የሚሰርቅና ስሜትን የሚያንጠለጥል እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ትኩረትን የሚጦልብ በየማዕዘኑ የምንኮመኩመው የወሬ ፍስክ ነበር።
ከአስተማሪዎቻችን አንዳንዶቹም የመወያያና የመደበሪያ እርዕሶቻችን ነበሩ። በተለይ የእንግሊዝኛ አስተማሪያችን ወ/ት እጸገነት ከነልብሰ ተክህኖዋና ተከለ ቁመናዋ አስተውሎ ለተመለከታት ተዘቅዝቃ የተሰቀለች የትምህርት ቤታችንን ባንዲራ ትመስላለች።

ከመልኳም፤ከሰውነቷም ገርጥታ ዘለግ ቅጥንጥን ያለች ስትሆን አጥንቷ ግን እንደ ‘ፌሮ ብረት’ ጠንካራ ሳይሆን አይቀርም፤ ጭራሽ ሥጋ የሚባል ነገር ብትንሹ ብቻ ነው፤በጅማት አወሳብቶ በስሱ ያለበሳት። ይባስ ብላ አዘውትራ የምትለብሳቸው ልብሶች ጥብቅብቅ ያሉ ስስ ናቸው። የሚገርመው ደግሞ ሱሪዎቿ ወገቧን ሰንገው፤ጭኖቿን ጨምድደው ከተጣበቁ በኋላ ከጉልበቷ መዳፈሪያ አንስተው እስከ እግሮቿ ቁርጭምጭምቶች ድረስ በሃይል ተንጠራርቶ ከተለጠጠ የጉማሬ አፍ ይሰፋሉ። ግራና ቀኝ በንፋስ ወይም በእርምጃዋ የጐድን እየተራገቡ እንደ ባንዲራ ይወራገባሉ። ‘ቬል’ የሚባለው፤ ‘ፋሽን’ ነው አሉ።፡

በእውነት እትዬ እጸገነት ያንን ተርፎ የሚያደናቅፋትን እራፊ ጨርቅ መመጽወት ብትፈልግ፤ከሁለቱ ቀንጃ ጥንድ አንድ ደህና አርጎ መቁረጥ ብቻ ሳይሆን መቀጠልም በሚችል ሁነኛ ‘መኪነኛ’ /ልብስ ሰፊ ቢሰናዳ አንድ አቅመ-አዳም ላልደረስ እረኛ ከሰውነቱ ጋር ልክክ ያለች እጀ-ጠባብ ይወጣው ነበር። እርሷም በሰማይም በምድርም መንገዷ ቀሎ ነፍሷም በጸደቀች።

ታዲያ ዛሬ ወረቱ አልፎ በዚህ ዘመን ደግሞ የዘመኑ ትውልዶች ከሰውነታቸው ጋር ተላትሞ፤የጭንና የባታቸውን ጥልፍልፍ የደም ስርና  የገላ ሸንተረር እንደ ምድር ባቡር ሃዲድ መስመሮች ‘በካርቦን’ እያሳዩ በቁማቸው ከአካላቸው ጋር የተሰፉና፤የተሳፋ ይመስላል። የማጥለቅና የማውለቁን ነገር በምናብ ስከስት ከወዲሁ ትንፋሽ ያጥጠኛል፤ላብም ይከጅለኛል። ቀጥዬም፤ እትዬ እጸገነት ስለዚህ ‘ዘመነ-አጣብቂኝ’ ምን ትል ይሆን ብዬ በህሊናዬ በጥያቄ አፋጠጥኳት፤ሃፍረተ ቢስ እና አይናውጣነቴን ስትታዘበኝ እያሳዩ የሚያሳጣና የሚዳኝ ሲሶ ሕሊናዬ በይሉኝታ እየወቀሰኝ።

በነገራችን ላይ በዚህ ዓመት ለስምንተኛ ክፍል ያልሆነ በሚል፤ብሄራዊ ፈተናን ‘ጠዳ ብዬ ልቀርብ’ ወስኛለሁ፤ እነሆ እኔም ከጅምላ ሻጭ ሳይሆን ሶስት ሜትር የውጭ ጣቃ አስቀድጄ፤በቁመቴና በወርዴ ተለክቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሰፋሁት ሙሉ ልብስ ሎተሪ የደረሰኝ ያህል በደስታ ያፍነከንከኛል። ሙሉ ልብሴ ረዥም ሱሪና ባለካምሱር (ባልና ሚስት ቁልፍ) ጃኬት ነው። ከውጭ የመጣ ጨርቅ ይመስለኛል ዓይነቱ ያልተዘወተረና ለስለስ ብሎ ጥንካሬው ከካኪና ገበርዲን የጠነከረና ሳይሆን አይቀርም ዋጋውም በዚያው ልክ ነው፤ ከነማሰፊያው የሰላሳ ፈሪ ብር ፈጅቷል።

በምርቃቱና በፍንጡር ስነስራዓት ላይ ለብሼ፤ ‘*ፕሎህ ይህድ!*’፤ ‘*በውሃ ይለቅልህ*’ በሚል አሰገራሚ ብሂል ተመርቂያለሁ። እኔም የአባትና የእናቴን ጉልበት ተነስቼ ከሳምኩ በኋላ የወንድሞቸንና እህቶቸን ጉንጮችም እንደነገሩ በአገጬ ‘ሞረድ፤ሞረድ’ አድርጌ ጸዳ ያለ መቀመጫ ፈለግሁና ለአንድ ሰዓት ያህል በትይዪ ተኮፈስኩ፤ የፍንጡር አረቂዬን በምላሴ እያጣጣምኩ በአፍንጫየም እየሰነፍጥኩ ሃሳቤ ወደ ተነገ ወዲያ መረሸ።
ከነገ ወዲያ፤መስከረም 17 በትልቁ የመገናኛ መድረካችን ከክፍል ጓደኞቼ የማገኘውን ሙገሳና ውደሳ በምናቤ እስል ነበር። ብዙም ሳላጎድፍና ሳላጐሳቁል ማቆትየን መረጥሁና፤ ወደ መኝታ ክፍል ገብቼ አውልቄ በጥንቃቄ አጣጥፌ ከትራስ ስር በላስቲክ አጅዬ አስቀመጥኩት፤ እነሆ ዛሬ ሶስተኛ ቀኑ ነው።

ከወንድ አስተማሪዎቻችን መካከል ጋሽ ሚኒያስ ሁሌ ከክረምት እረፍት ሲመለስ በግምባሩ ላይ እንደኮፍያ ፊት ለፊት አሞጥሙጦ በጣም ሹሎ እንደተቀረጸ እርሳስ ሲመስል በኋላው የሚሞለሞለው ጸጉር ደግሞ እስከማጅራቱ መፈጣጠሪያ እየተመነደገ ያድግና የአገራችን መደዴ ተራራ ይመስላል።እንዲያውም ፊትና እራስ ቅሉ ሳጥናዔላዊ አለዚያም ‘ኢሮዲናሚክ’ ቅርጽ ይመስላል።

ታዲያ የሚገርመኝ ከተደመደመው የጸጉር ክምር ያፈነገጠች አንዲት ዘለላ ጸጉር እንኳ መቃናት የምታነቃቸው ሁለት እጆቹ  በየአምስት ደቂቃዎች እየተፈራረቁ እንደ መኪና መስተዋት ዝናብ መጥረጊያዎች ከመዳፉ ጎድጎድ ብለው በተሰደሩ ጣቶች እራሱን በየአቅጣጫው እየተንሳፈፉ ይተመትማሉ ። አንዳንዴ የትምህርቱ ይዘት ቀልብ የሚስብ ካልሆነ በአንድ ክፍለ ጊዜ የሚያደርገውን የእጅ ትምተማ ብዛት ስንቆጥር እስከ 20 ይደርሱ እንደነበር አስታውሳለሁ። ይኸን ያህል እንክካቤ የሚጠይቀው ጐፈሬ ‘ጆንትራ ቮልታ’ የሚሉት ቄንጥ ነው አሉ። በዚህ ውበቱ ብዙ እንስት ተማሪ አስተማሪዎች እየተጠቋቆሙ ሲሽኰረመሙበት አይቸ ቅናት ድብን ያደርገኝ ጀመር የጐረምሳ ነገር።

ቅናት ያደረበት ልቤ ዳግም ጸጉሬን ክምክም ላልቆረጥ ወይም እንደ ከተማችን መደዳ ባህርዛፍ፤ እንደ ጠፍ ጫካ አላሳድግም ብዬ አመጽኩና በእንጨት ሚዶዬ (ማበጠሪያ) ከእጆቼ ጋር እያቀናጀሁ ጸጉሬን ወደ ፊትና ኋላ ያድግ ዘንድ መግራት ጀመርኩ። በሳምንታት ውስጥ የአላፊ አግዳሚውን ዓይን ይሰርቅ ጀመር፤ወዲያውም አባቴ ይኸንን እንግዳ ነገር በአግራሞት አስተውሎ  ኖሮ፤ *‘ልጄ ይሽ እንደ በግ ላት ጸጉርን ወደ ኋላ ማሳደግ ምን የሚሉት አባዜ ነው?* ብሎ በተግሳጽና በምክር እንድላጨው ተደረገ። በማግስቱም የእራስ ቅሌ መቅለልና መሾል እትዬ እጸገነትን ሳይስመስለኝ አልቀረም፤  የጓደኞቸን ትረባ እየገመትኩ፤ ፈራ ተባ እያልኩ ዘወትር ወደማልቀርበት ት/ቤት ሄድኩ።

 አሁን በምገኝበት ዘመንና ሃገር ጸጉሬን አሳድጌ፤አበጥሬ፤አንጠባርሬ፤ብፈልግ ቁንዳላ (ጉንጉን) ብሰራ ከልካይ የለኝም። ነገር ግን ከግምባሬ መዳረሻ ያለው በራዬ እንደ ሳህራ በረሃ በየዓመቱ እየሰፋ ሄዶ የፊቴ ወሰን በጣም ገፍቶ እንደ ‘ክልል አንድ’ እየተለልጠጠ በማናለኝበት ሰፍቷል። ግምባሬ ላይ የነበረው ድሮ አንዳንድ ሰዎች ጥቁር ሃር፤ዞማ ጸጉር እያሉ የሚያሞካሹት የጎልማሳነት ጸጉሬ ዛሬ ወደ አገጨና ጉንጮቸ ዳርቻ ስር ሰዶ የሻገተ ከርዳዳ፤ ጉራማይሌ ጢማም አድርጐኝ አረፈ እንጂ። ‘አገር ሲያረጅ አረማሞ ያበቅላል’ ነበረ የአበው ተረት።

በትዝታ ሰምጬ በራዬን እያሻሸሁ፤ጺሜን እያጠማዘዝኩ ሃሳቤን ሳጠነጥን አንድ የቅርብ ዘመን ወሬ ሳልፈልገው በቀኝ የህሊና ቁራኛዬ ጥንቅር አለብኝ፤ ‘ነፍሳቸውን አ/ይማረውና’ የሞቱት ወይም እንደ አንዳንዶች እምነት ‘ያረጉት’ ጠ/ሚኒስቴር አቶ መለስ የህዳሴን ግድብ ዲዛይን (ንድፈ-ሃሳብ) ያፈለቁት እየሰፋ ከመጣው ባዶ እራስ ቅላቸውን ‘በምርቃና’ ሲያሻሹ ቱግ ብሎላቸው ነው ይባላል።

በእነዚህ አራምባና ቆቦ የሚራራቁና የማይዛመዱ የልጅነትና፤የግልምስና ሃሳቦች ሳንቀሳብል በአግባቡ ሳልተኛ አድሬ ሲነጋጋ ድካም አብቶ ረትቶኝ ኖሮ ወደ አራት ሰዓት ተኩል እያሸካኩ በሚዳሩ፤በሚባረሩ የደሮ መንጋና ሁካታ አስደንብሮ አስነሳኝ።

እንዲህ ሃሳቤን በምናቤ ጠባብ መስኮት ሳያንኳኩ ተንጋግተው ገብተው በድካም ዝሎ በተጋደመ ገላዬ እየተፈራረቁ ሲረመርሙኛና ሲጋልቡኝ ያደሩትን የህልም ደባሎቸን ከብርድ ልብሴ ጋር አራግፌ ተነሳሁና አንድ ዳጎስ ያለ መጽሃፍ በግራ እጄ ብብት አጣብቄ ሁለት እጆቼን በሱሪየ ኪሶች ከትቸ ንጹህ አየርና መጤ ሃሳብ እያሳደድኩ በአካልም በመንፈስም ከተማና መንደራችንን አቋርጬ ወደ ምዕራባዊ አቅጣጫ አዘገምኩ። በመንገድ ዳርቻ የተኮርቱትን ጠጠሮች እግሬ እንደ ቀናው ባልንደረደርም እንደ ግሩም ኳስ ተጨዋች በቆረጣ/በጠረባ እያኳተንኩ አቀናሁ። ይኸ ዘይቤየ ከየአቅጣጫው የሚቀባበለውን ረዥም የሰላምታ እንካ ስላንታያን ያንን ተከትሎ የሚግተለተለውን የመንደሬን ሰው አድካሚ ጥያቄዎች ላይ እንደ ጎረምሳ በማመጽ የማደረገው  ድብብቆሽም ነበር።

በመስከረም ወር አጋማሽ በጠዋት ገስግሳ በምስራቅ ደምቃ የወጣችው ጀንበር ከአናት ትይዩ አልፋ ወደ ምዕራብ እያጋደለች ወደ ማደሪያዋ ሳይመሽባት ልትመስግ ትጣደፋለች። የጮራና የሙቀቷ ኃይል ለስለስ ብሏል። የቀኝ እጆቸን ጣቶች በመደዳ አሰልፌ መሃል ግምባሬና መንታ ቅንድቦቸ መጋጠሚያ ላይ ጠድቤ እንደ ሰነፍ ወታደራዊ ሰላምታ ዓይነት ዓይኔን በመጠኑ ጨፍገግ አድርጌ ገላመጥኳት። ጫማዬ አውራ ጎዳናውን ለቆ በለስላሳው አረንጓዴ የሳር ጉዝጓዝ ላይ ኰቴ ሳይፈጥር ሲዘናፈል ተሰማኝ። ገማሽ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በከተማዋ ምዕራባዊ መዳረሻ ከተንጣለለው አረንጓዴ መስክ ላይ የተሰባጠሩ እንስሳት ውበት ማርኮኝ እንድቀርባቸው አንገላጀጀኝ። በጫማዎቼ ጠርዝ የጣመነውን ጭቃ ለማስወገድ እግሮቸን ወደ ጎን እያንሻፈፍኩና እያንሳፈፍኩ በግራ በቀኝ ጫሞቸን በሳር ሞረድኳቸው። የሌሉት ቁር በሚፈጥረው ጤዛ አለዚያም ከዝናብ እንደ እንባ ዘለላ አቀርዘው በሳር ቅጠሎች ላይ የሚታዩት የውሃ እንክብሎች ሁሉ በጸሃይዋ ሙቀት ተነው ወይም በመንጋው ዱካ ተራግፈው መሬቱን  አውዝተው ቅባት እንደጠገበ  ዞማ የሚመስለው አረንጓዴ ስጋጃ በሚማርክ ድንቅ ተፈጥሯዊ ፍቅር እግሬን ቀይዶ፤ እይታዬን አደንዝዝ አካሌንም በአንዳች ምትኋቱ አስንፎና አዝለፍልፎ ጣለኝ።

በሆዴ ተንበልብዬ የእጆቸን ክርን ከመሬት አንጥፌ ከወገቤ በላይ እንደ ኮብራ እባብ ተቀስሬ ወደግራና ቀኝ እየቃኘሁ ሳስተውል በሰፊው ሜዳ ላይ እንደየፍጥርታቸው ተወሳብተው ምድር በሰፊው ማዕድ ያቀረበችላቸውን ጸጋ እየተቋደሱ የሚፈነጩ ከብቶች፤ፈረሶች፤በጎችና ፍየሎችም ጭምር አምላካቸውን በዳንኪራ የሚያመሰግኑ መሰሉኝ።

በአቅራቤዬና የእጄ መዳፍ ከተነጠፈበት ጀምሮ በዙሪያ ገባዬ፤ፊትለፊት የሚታየኝን የተፈጥሮ ውበት በአንክሮ ማድነቅ ጀመርኩ። አፈር፤ማዕድን፤ውሃ፤ ሙቀትና ቅዝቃዜ ተዋህደው ተፈራርቀው እንደዚህ እጡብደንቅ የሆነ የተፈጥሮ ፈርጥ አብቅለው በማንጠፋቸው የፈላስማ ያህል እጅግ ተደነቅሁ።

ቅባ ቅዱስ እንደተቀባ የሚያፍለቀልቀው አረንጓዴና ወዛም ሳር በየመካከሉ እንደ ጉራማይሌ ንቅሳት ተወሳብተው የሚፈጥሩት የጸደይ አበቦች ውበት አይንን መንፈስን የሚያነሆልሉት እኔን ብቻ አልነበረም።  ይኸ በቃል ለመግለጽ የሚያስቸግር የአበቦች ሕብረቀለማት ንቦችንና ቢራቢሮዎችንም እየሳቡ አፍዘው አደንግዘው በቁም የሚያስቀሩና ማዕዛቸውን እንደተቋደሱ ደስታቸውን በዜማና በዳንስ የሚገልጹበት ሚስጥር ነገር ሁሉ የውስጤንም የውጩንም አይኔን ማረከው።

ከወገብ በላይ ያለውን ክብደቴን መዝነው እስካን የተሸከሙት የእጆቸ ክርን ደክሞ ሲጣምነኝ በጀርባዬ ዞሬ ተንጋለልኩ። አይኖቼ በዙሪያ ገባዬ ከማስተውላቸው አድማስና አጽዋት በመጠቀ እርቀት ላይ ቀልቤ እይታዬን ተከትሎ አሻቀበ፤መንፈሴ ሁሉ ወደ ጠረፍ ተንቧቸ።

ከሰሜን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ጉምና ደመና እያሰባሰበ የሚነዳው ንፋስ በምድር በግና ከብት ከሚያንጋጋው እረኛ ጋር ተመስሎ ታዬኝ። ጉምት የሚያህል ደመናዎች ህዋውን አጋምሰው ሲትመለመሉ እየራቁ በሄዱ ጊዜ እንደ ጥጥ ባዘቶ ሳስተው የሥጋ ሞራ ያህል ትንሽ ነጠብጣብ ሆነው ዓይኔ አስባስቦ መከተል ሲያቅተው ሸኝቶ ይመለስና እንደገና በሌላ አቅጣጫ ሌላ ደመናዎች ያሳድድ ጀመር።

በመካከሉ በሚፈጠረው ክፍተት የዓይኔ ቁራኛ ወደ ኃብረ ሰማያዊው ኃዋ ጓዳ ዘው ብሎ ሲጠልቅ አንዳንድ ብርሃናቸው የደበዘዙ ከዋችብቶች እንቅልፍ እያንገላጀጃቸው አይናቸውን በትንሹ እንደጨፈኑ የጸሃይ ግልግሎች መስለው ይሰተዋሉኝ ጀመር። አይ የእረኛ ነገር ከከብትና እንስሳ ሌላ የምመስልበት በአካልም በእሳቤም የማንጣጥረው ተምሳሌ አጠጠኝ።

ነገር ግን በተወሰነ ቅጽበት እይታዬም ሃሳቤም የሚያንጎላቹትን ከዋክብቶች ጎልቷቸው አለፈና ወደ ውስጥ እየኳተነ መጠቀ። ከአይኔ ይልቅ ምናቤ ተሽቀዳድሞ እየገሰገሰ የአቀበት መንገድ ድሮውንም አይመቸኝምና ትንፋሽ ቁርጥ፤ቁርጥ እስኪለኝ ድረስ አሻቅቤ መረሽኩ። አሁን ግን የጣመነኝ ከንዴን፤ወገቤን ወይም እግሬን ሳይሆን የራሴን መፈጣጠሪያ ማጅራቴንና 'ዓይነ-ስቤን' ነበር።

ዓይኔም ምናቤም ተቀናጅተው የሚጭብጡት የሚያርፍበት ግዑዝ ነገር ሲያጥጠኝ አንዳች ትልቅ ነገር በፍራተ ህሊናዬ ተገማሸረ ፤ እነሆ የፈጣሪያችንን ግቢ የደፈርኩ መሰለኝና ኃፈረተ ልቦናዬ ፈርሃ ፈጣሪየ የገሰጻኝን ያህል ወደ ኋላ አጠነጠንኩ ቀልቤም እይታየንም ተቻኩዬ ቀየድኩት።

ወዲያውም ሌሎች በርካታ ድምጾች በዙሪያዬ እየተበራከቱ መጡ በሜዳው ደቡባዊ የመጨረሻ ዳርቻ በሚውርደው የበጋ ምንጭ የክረምት ወንዝ እረኞች በዋናና በጨዋታ እየተወባሩ ይንጫጫሉ። አልፎ፤አልፎ ዋሽንት የሚነፉ፤ጅራፍ የሚወነጭፉ የሚጠራሩ እረኞች ይሰማሉ። ከሁሉ የበለጠ ደግሞ የተቃራኒ ፆታውን ሽንት አነፍንፎ ጉያዋን በአፍንጫው ዳጎስ አድርጐ ለምቦጩን በማሾፍ ዓይነት በየአቅጣጨው ለጥጦ የሚያክላላው የጋማ ከብት ቅጥ ያጣ ጩኸት የጸጥታዬን አንቴና አናጠበው፤ትኩረቲንም ወሰደው ።

አድራጎንቱና ድምጹን ስሰማ ስንኝ ድርድሮ የፍቅር አድናቆቱን እየገለጸ ይሆን ብዬ በሃሳብ ስኳሽ የመሬቱ ቅዝቃዜ ልብሴን ዘልቆ አጥንቴን ቆረጠመውና ከሚሻሙኝ የሃሳብ መንጋዎች ተንገዳግጄ በመነሳት ከሜዳው ባሻገርና በአጐራባች ያሉትን አድማሶች መቃኘት ጀመርኩ።

ረፋዱ አካባቢ የኰበለልኩትን ከተማና መንደር አቅጣጫ ስመለከት ጅብ ባሉ የባህር ዛፉ ጫካና ቤቶች መካከል እየተርመሠመሠ የሚጓፈጥ ጢስ በየአቅጣጫው ይታየኝ ጀመር፤ ኃሳቤ ገስግሶ ወደ የሰው ጓዳ እየቀላወጠ በየጐልቻው የሚሰማንነውን ሳስብ አፍንጫየም የሚመኘውን መዓዛ ያሸት ጀመርና የረሃብ ወስፋቴን አራወጠው በፍጥነት ወደ መጣሁበት ለመመለስ ሃሳብና ጉልበቴን ሳሰባስብ የቆሁበትን ውብ ሜዳና ዙሪያ ገባ በድጋሚ በአድናቆት ስገላምጥ ራቅ ወዳለ አካባቢ የማየው ነገር ትኩረቴን የበለጠ ሳበው፤ ጀምበሯ ወደ ምዕራብ እዘቅዝቃለች ሙቀቷም የለሆሳስ ነው ዙሪያ ገባውን ንፋስ በሽውታ ይዳስሰው ጀመር።

በአራቱ ማዕዘን ተገማሽረው ወደ ኃዋ የተመነደጉት መደዳ ተራራዎች ጫፋቸው በደምና ተሸፍኗል ከአድማስ ባሻገር ጥቁር ደመና ያረገዙ ሰማይ የዝናብ መቃረቡን ያበስራል የእነዚህን በአራት ማዕዘን ተራራዎች ከደመና ጋር ተወሳብተው ሳስተባቃ ሰማዩን የተሸከሙ ጽኑ ምሰሶዎች መሰሉኝ።

በነዚህ ሃሳቦች ተቀይጄ ዓይነ ልቦናዬ አድማስ የብስ አልፎ ሲጋልብ ቢቆይም አካሌ ግን በድኑን ቀዝቃዛ ሳርምድር ላይ ለሰዓታት የቆዬ ስለሆነ ለማፍታት በሃይል ተንጠራርቸ ስወራጭ ከተኛሁበት አልጋ ወድቄ ላብ በላብ ሆኘ ባትቸ ተነሳሁ።

አቅሌን ገዝቸ ዙሪያ ገባውን ስቃኝ ከአልጋዬ ጎን ያለው 'ዲጂታል ሬዲዩ' ሰዓት እንደ ትንሽ ትራፊክ መብራት ደምቆ 3:45ኤም ይላል፤ ከንጋቱ ለአሥር ሰዓት ሩብ ጉዳይ መሆኑን በአበሻ ሰዓት አቆጣጠር መንዝሬ ተረዳሁ፤በህልሜም፤በቅዠቴም፤በእውኔም አበሻኛ እየተቃኘሁ።

በሕልሜ የጀመርኩትን መንጠራራት በእውኔም ቀጠልኩበት፤ሳቅም፤ግርምታም እየተፈራረቁብኝ፤ከድንኳ አልጋዬ ጠርዝ አፈትልኰ ከእንጨት ጣውላ ወለል ላይ በደረቀው ሌሊት ተዘገረርኩና።

አስቀድሜ ስፈራገጥ የገፋሁትን በወፍ ላባ ተሰግስጎ በቀላሉ የሚኮበልለውን (መከነፍ የሚቀናውን) ቀትረ-ቀላል ባለቀረጢት ብርድ ልብስና አብሮት የኮበለለው አንሶላ በከፊል መደላድል ሆነው አካሌን ከደረቅ አንጨት ልትሚያ አለዘቡት፤የግዑዝ ብርድ ልባስና ምንጣፍ ጉዝጓዝነት እንደ ውለታም እየተሰማኝ ጭሙቅሙቅ አድርጌ አቅፌም፤ተኮናንብኩና ካቆምኩበት ልቀጥል እንቅልፍም ህልምም ተማጠንኩ አንዳቸውም ዝር ሳይሉ በቁጭትና በብስጭት ካልጋዬ ተመናጭቄ ከሰዓታት በኋላ ተነሳሁ። የደረብኩትን ብርድ ልብስ በቀኝ እጄ በተቃራኒው የአልጋ ጎን አልፎ እስኪዘረር ገፈፌ እያምዘገዝግሁ።

በሃገሬው 'ባዕድ ቋንቋ' ስድብ በቁጣ እየቀናኝ ፤በአማርኛ ሲመነዘር 'ዘራፍ' ማለት ሳይሆን አይቀረም።

በዘመንና በቦታ ወደ ኋላ አጠንጥኜ የሃሳብና የትዝታ ፋይል እንዳንኮባች የገፋፋኝን እውነታ ስመረምር ከጸሃይ ብርሃን፤ከውብ የተፈጥሮ ጸዳል ጋር አጎናጽፎ ስቀማጠልበት የቆሁት ሜዳ በዓመድ እንደተዳፈነ የእሳት፤ የሚያቃጥል ረመጥ ሆነብኝ፤ መንፈስንም፤አይንንም የሚሳጭ የአገጠጠ የምድር ተውኔት ተጋፈጠኝ። እስካገኛቸውው የምናፍቃቸውው፤በደስታና በፍቅር የማልማቸው የመንደሬ፤የአገሬ ሰዎች፤የአብሮ አደጎቹ ሳቅና ፈገግታ በሚያኮማትር ሃዘን ተቅይሮ በጠለቀ ትካዜና በቁጭት ተውጠው ይታዩኝ ጀመር። ውሎ- አዳሩ አጥሮ የሚቀጥለውን ቀን ለማዬት ሌሊቱ እስኪነጋ በደስታ ቃትቸ የማንቃቃው 'ደግ ቀን' እነሆ አሁን ሌሊቱ ተለጥጦ ቢረዝም እስከናካቴውም ባልነጋ በሚያሰኝ ዘመን ተተክቷል።

ወደዚህ የህልምና ቅዥት ማዕበል በህልም ጀልባ ስቀዝፍ የጊዜና የቦታ ኬላ ተሻገርኩና በጎርፍ ተጠራርጌ ከመወሰዴ በፊት የሰማሁት፤ያወቅሁት እውነታ በምናቤ ተሰንቅሮ ኖሮ በድን ገላዬን አጋድሞ መንፈሴ በህልም ሕዋ ምህዋር ሲባዝን የደከመ አካሌንም አንገጣውሮ አወዳደቁን አከፋው። ስለ አገሬ ኢትዮጵያ እንደምንጊዜውም ሁሉ ከሥራ መልስ አልጋዬን ሙጥኝ እንዳልኩ ከታመኑ የዜና ድህረ ገጾች፤ሬዲዮ ጣቢያዎችና በተለይም ከኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንና ሬዲዩ (ኢሳት) ስለ አገሬ ውሎ አዳር ሳልሰማ እንቅልፍ አይወስደኝም። እነሆ ዛሬም የሰማሁት አበሳ የወገኔ ሲዖል በወያኔ የማፊያና አፋኝ፤ገዳይ ቡድን የሚፈጸምበትን መከራ ለሰዓታት በሞባይል ስልኬ ሳዳምጥ ቆይቸ የውል እድር እንቅልፍ አብቶ ከጣለኝ በኋላ በሕልምና ቅዥት ማዕበል ቆዝሜ ተነሳሁ።

ትናንትና ስለ ሀገሬ ጉዳይ ስንኝ ስቋጥር ጎኔ አልጋዬን ጠርዝ የነካው ከንጋቱ አሥር ሰዓት ላይ ነበር፤ከዚያ ባለፉት ቀናትም፤ሳምንታትም እንደዚሁ ነበር።

ታዲያ ዛሬ የተባበሩት እንቅልፎች ረትተው ጣሉኝና በልጅነት ህልም አማለው ዘመኔን፤መንዲሬን፤ትውልዴን በንፅፅር፤በስመመን ያስቃኙኝ ጀመር። ወደ እውነታው ስመለስ ግን የሚሆነው ሁሉ እጅግ የከፋ የመረረ ቅዥትና መጥፎ መርዶም ነበርና እንደ ወረደ ሰማሁት።

**የዕለቱ ‘መርዶ’፤ ዜና፤**

- የወያኔ መንግሥት ወታደሮች ንጹሃን ዜጐችን በተለያዩ የአገሪቱ ‘ክልሎች’ በጠራራ ጸሃይ አነጣጥረው በጥይት ገደሉ፡
- የሰባት ዓመት ሕፃን ሐረር ከተማ ከወያኔ ፓሊስ በተተኮሰ ጥይት ከእናቱ እቅፍ ላይ እራሱን ተበርቅሶ ሞተ፤ እናቱንም ክፉኛ አቆሰሉ፡
- የወያኔው መንግሥት ደርዘን ኢትዮጵያዊያንን በቴሪሪዝም ስም እድሜ ልክ አሰረ፤አስፈረደባቸው፤
- በአዲስ አበበአ ዩኒቨርሲቲ ወጣት ተማሪዎች መካከል፤ ኦሮሞና ትግራይ በሚል ዘር ቁርሾ በተነሳ ጠብ ሰበብ ግቢውን የተቆጣጠረው የስለላና ታጣቂ ሃህል አድሏዊይ ድብደባ፤አስራት፤ግርፍት፤በተለይ በኦርሞ ተማሪዎች ላይ በጅምላ አባረረ፤ (፡

**የከረመ የመከራ አዙሪትና አባዜ ወደፊትና ወደ ኋላም ሲጠነጠን ደግሞ ከዚህም የከፋ ነው፤ ከመርዶ ማምለጫ የለም፡-**

- በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አማሮችን ወደ መጣችሁበት ሂዱ ብሎ በገዳይ ታጣቂዎችና፤ በወያኔ ሰንሰለት በተዋረዱ ለሚገኙ የአካባቢና የክልል ባለስልጥናት በተላለፈው ቀጭን ትዕዛዝ መሰረት የፌዴራል ወታደር አዝምተው አፈሙዝ ተደቅኖባቸው እየተዋከቡ፤ወልደው ከብደው ከኖሩበት፤እትብታቸው ከተቀበረበት ቄዬ፤ነፍስ ጡር ሳትቀር፤በግፍ እየተገፈተሩ እንደ ዕቃ በካሚሆን እየተጫኑ ተጋዙ፤በእግር ኳትነው ተባረሩ፤ የሃገርና የዜግነት ምንነት ምን ፋይዳ የለውምና በእኝ ሐገር፡
- ለዘመናት የለፉበት ሃብት፤ንብረትን፤ተነጥቀው፤የተሰለፉበትን የንግድ፤ሙያ፤ትምህርት አቋርጠው እንደ ባዕድ ተቆጥረው አማሮች ናቹህ ተብለው ከቤሻንጉል ተባረሩ፤ ጎጃም ክልል ባዶ ማዳና ጫክ ውስጥ ተደፉ፤በማጅ ዞን ጉራፋርዳ፤በአፋር፤በሶማሌ ክልል፤በጋምቤላ፤አምናም ዘንድሮ እንደዚሁ፤
- ብዙ መቶ ሺህ ወጣት ዜጎች በአገራቸው እንደ ሁለተኛ ዜጋና እንደ ባዕድ በመታዬታቸው፤የበይ ተመልካች በመሆናቸው ከባዕድ አገርስ በምን ይለያል በሚል በባህር፤በየብስ ሲሰደዱ የሚሞቱት፤የሚሰቃዩት፤ሕይዎት እጣ ፈንታችን/ው የምድር ገሃነም ሆኗል፤ለጥቂቶች ድሎት፤ስልጣን መደላድል ንቅዘት፤ክብረት፤ሲባል።
- ድንቁርናና እልህ ያደለበውን ግብዝ መንግሥት እንመክራለን፤እናስተምራለን፤ወገናችንን፤እምነታችንን ከተደቀነበት መከራ መፍትሄ እንሻ ዘንድ ጥብቅና እንቆማለን ብለው፤ፍጹም ሰላምና መፍትሄ አንግበው መንግሥትን በሰለጠና ውይይት በጋበዙና በተማጠኑ የእስልምና መፍትሄ አፈላላጊ ወንድሞቻችንን አንገላቶና አዋክቦ ቃሊት ዘብጥያ ካወረድ በኋላ ‘አኬልዳማ’ ድራማ እየሰራ ንጹሃን ዜጎቻችንን በእስር ቤት ያማቅቃል፤ወላጅ፤ቤተሰቦቻቸውን በድቅድቅ ሌሊት አጥር አፍርሶ፤በር በርግዶ በመግባት እያሸበረ እንቅልፍና ሰላም እየነሳ መብት ይገፋል፤ ንብረት ይዘርማል። ከዓመት በላይ በስልጡንና ሰላማዊ ጥያቄ ‘**ድምፃችን ይሰማ**’ ባሉ፤ ምላሹ እብሪት፤ጥፋትና ግድያ ሆኗል።
- ድሮ ‘የተማረ ይግደለኝ’ የሚባል ሚስጥራዊና ፈሊጣዊ አባባል ነበር፤ዛሬ ግን ‘የተማረ ይገደል’ በሚል የተተካ ይመስል የሃገራችንን ምሁራንና ተማሪዎች በባሌና በቦሌ እየጎረፉ ምድራችን የማይምነት ጨለማ ነግሶባታል።
- በዘመናችን ዓለም በሙያቸውና በችሎታቸው እውቅናና ክብር የሰጣቸው በርካታ ጋዜጠኞች፤ምሁራን፤ባለ ራዕይ የፓርቲ መሪዎች፤ንጹህና ምስኪን ዜጎች በእድሜ ይፍታቹህ እሥርን በየማጐሪያው ተውረውርው በአበሳ ይማቅቃሉ።
- በምርጫ ፱፯ ማግስት፤ድምፃችን አይነጠቅ፤በመረጥናቸው እንተዳደር ባሉ ሰላማዊ ዜጎች በአገራቸው መዲና በጠራራ ጸሃይ በጥይት በጨካኙና ፈሪው የወያኔ አመራር ትዕዛዝና በአጋዚ ጦር ጅምላ ጭፍጨፋ ከጣሊያን ፋሽሲት የመርዝና መትረዬስ ግድያ ወዲህ ለሁለተኛ ጊዜ በድቃላ ፍናዎቻቸው እነሆ አዲስ አበባ በድም ጎርፍ ታጠበች፤ ሺህዎች በካሚዎን ተጭነው ወደ በርሃ፤ጫካ እስርቤት በግፍ ተጋዙ፤ [እነርሱ]፣ ወያኖዎችና ቁንጮዎቻቸው፤ በሸራተንና በሸርክ ባሰሯቸው ሆቴሎች ጥዋቸውን በዋንጫቸው ደም ቸለሱ፤በሶዶምና ጎሞራ አስረሽ ምችው የጥፋት ዳንኪር ተቃኝተው አታሞ እየደበደቡ።
- በየጐዳናው ዳርቻ የወደቁትንና በሆስፒታል ደርሰው ህይዎታቸው የተቀጠፉትን ልጅ፤ወንድም፤እህት፤እናት አባት ቀሪ ወገን በውል እድሩ አልቅሶ ሊቀብር የተጠየቀውን የመግድያ ጥይት ዋጋ አስከፍለው አስከሬን ቢረከቡም አልቅሰው እንዲቀብሩ፤ሃዘነአቸውን እንዲገልጹ አልተፈቀድም፤ ብዙ አናት አባት ያለጧሪ ቀባሪ ቀርተዋል፤በርካት ህፃናት ወላጅና አሳዳጊ አጥተው በየጐዳና ወድቀዋል።
- እነሆ [እነርሱ] ገዳዮቻችን ግን የመተትና የጥፋቱን እራስና ቁንጮ ፤ከቤተ መንግስትና፤ ቤተ መቅደስ፤ ገዳዮቻችን፤ ገዥዎቻችን አርጅተው፤ጃጅተው ነቅዘው ሲሞቱ አገር በድፍን ማቅ ለብሶ፤ብሄራዊ ለቅሶ ተደግሶ ለሳምንታት ሌት ተቀን አልቅሳችሁ ኀዳናውን በእንባ እጥለቅልቁ፤ደረታችሁን በቡጢ እየደሰቃችሁ፤በሃዘንና ቁዘማ እንድትማቅቅ በሚል በአፈሙዝ ያስገድዱናል።
- ዋና ሃገራችንን፤ቤታችንን መሰረት በደቦ አናግተው፤ስር መሰረቷ እንደላላ ማገር ስበው፤ጣራ መዘው፤ግድግዳም ነቅለው አዲስ ጐጆ ያወጧት የበኩር ልጅ፤ ኤርትራ ጋር የወረት ፍቅራቸው ሲያልቅ፤ፍቻቸውና ክፍፍላቸው ባስነሳው አታካራ ጠብ ጭረው በቆሰቆሱት ጦርነት ሞቶ ሺህ ምስኪን ወገኖቻችንን ማገዶና ደመ-ከልብ አድርገው አስቀሯቸው፤ ስንቶች ወላጅ ጧሪ ቀባሪ፤አሳዳጊ አጡ።
- ሽለ ሙቋ ሃገር በአፈሯ የምታሸተው፤በከርሰ-ምድሯ የምትቸረው ድንቅዬ፤ብርቅዬ የከበረ የማዕድን በረከትና ስጦታ ሁሉ ለነገ ሳይሉ ዘርፈው በጥቁር ገበያ የሚቸበችቡት፤በልመና እና በትውልድ አራጣ የሚገኘውንም ቢሊዮን ዶላር ብድር በሙስና እያስኰበለሉ የሚዘርፉበት የውጭ ሂሳባቸው ሞልቶ ሲጨናነቅ አገርና ሕዝብ ተራቁቶ እራቃኑን፤ጦሙን፤ውሎ ያድራል።
- ለሃያ ዓመት ዘርፈውና ሸምተው ባቀኑት በታጠቁት መሳሪያ ሲግድሉን፤ኑረው አናልቅ ብንላቸው ሌላ የጅምላ ጥፋት፤ ከግብጽ ጋር የጦርነት መዘዝ እየሳቡልን ናቸው፡ የኢትዮጵያ አባይን የመጠቀም ተፈጥሯዊ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የግብጽም የሺህ ዘመን የስልጣኔያቸው፤የሕይዎታቸው፤የህልውናቸው መሰረት መሆኑ አይካድም። ታዲይ ይኸንን የዓለም አቀፍ ድንጋጌ የሚፈታውን ጉዳይ፤ድሮውንም ከሕዝም ሳይመክሩ፤ጥቅምና ጉዳቱ ለአገር ዘለቄታ በብቁ ባለሞያዎቹ ስለመጠናቱ በአግባቡ ሳይገለጽ ለፓለቲካ

ፍጆታ ማዋያ እንድውል ብቻ ታስቦ የሕዝቡን ታርካዊና ብሄራዊ ስሜት በማማለል ከነጋዴው ወረት፤ከሰራተኛው የዕለት ጉርስ፤የእናት መቀነት ሳይቀር እያስፈቱ በሱዳን አዋሳኝ አንጋዳ እየማሱ አባይን እንገድባለን፤እናቅባለን ይላሉ።

ስለጉዳዩ ያልታምከረው፤ዜጋ በተለይ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊና ትውልደ-ኢትዮጵያዊ፤ ሺህ ሰላማዊ ዜጐችንን አጉሮ፤በአሰቃቂ ስቃይ የሚቀጣ ቡድን፤እንደ ጠላት በሚያየው ሕዝብ ማንን ሊያታልል ነው? ዛሬ 'የአዛኝ ቅቤ አንጓች' መስሎ የሚንደፋደፈው በመሸ ሰዓት፤ ይኸንን አይን ያወጣ ዝርፊያ ተከትሎ የደርሰውን የኑሮ ቀውስ በመቃወም የመሰብሰቢያ አዳራሽ ፈጽሞ ሲያሳጣቸው፤ለሁለት ዓመት ተቦጥቡጦ ከዝሪፊያ የተረፈው ቅንጣት ገንዘብ ብቻ ሲሆን፤ የአባይን ተፈጥሯዊ መውረጃ መቶ ሜትር አስቀየስን' በሚል የግንቦት ፳ የፓለቲካና የፕሮፓጋንዳ ዜና የሚያናፍሱ። ይኸ ድንገተኛ ዜና ስጋት ያሳደረባት ግብጽ ስጋቷን፤ጠቧን፤ስትዶልት መንግሥቷና ተቃዋሚዎቿ ልዩነታቸውን ወደ ጎን አድርገው ሲያሰሩብን በአደባባይ ተደመጠዋል።

- ይሁንና ከዲፕሎማሲያዊ ምክክርና ውይይት ባለፈ፤ወያኔ የጦረኛ ከበሮውን መደለቅ ጀምሯል፤አቅም ባይኖረንም አባይ በሕዝቧ አጥንትና ደም ይገደባል አይነት የጀብደኝነት ፉከራን ቀረርቶ አብዝቷል፤ እኛን ጦር ማግደው እነርሱ ውጭ ሆነው ባንክ ያደለቡትን ዶላር እየኮመኮሙ በእልቂታችንን ሊዝናኑብን ይሆን?

  ኸረ ለመሆኑ የዚህ ህዝብ አምላክ፤ወገን፤ፈቃጅ የለውም ይሆን?
  ይኸ ሁሉ አበሳና መከራ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞልቶ እየፈሰሰ እንዲትስ ያስተኛል?፤ለምንስ በቀን አይስቃዥ?

***ኸረ ለመሆኑ 'ወያኔ' ትውልዱን፤አስተዳድጉን፤ታሪኩን፤ተግባሩንና ምግባሩን ረስተን ነው ግራ የምንጋባው***???

ወያኔ፡ ድልድይ አፍርሶ፤
ባንክ ዘርፎ፤በጣራችን እሳት ለኩሶ፤
ነፍስ ቀጥፎ፤ተቋም ደምስሶ፤
ባህል፤ ታሪክ አርክሶ፤
አይደል እንዴ ! የዘመተ፤የሸፈተብን ከጠላት ብቀላ ወርሶ።

ቃል የበላ፤ መሃላ፤ ያጎረሰ እጅን ነክሶ፤
የሃገር ሠራዊት የበተነ ጉድጓድ ምሶ፤
በፈሪ ድላው ደብድቦ ውርደት አላብሶ፤
አገር ገንጥሎ፤ ድንበር ቆርሶ፤
ባንዲራ አንኳሶ፤
ከጠላት ሸር ደግሶ፤
በፋሺስት ባንዳ ሽንት ርሶ፤
በጠላት ፍግ በቅሎ በስብሶ፤
በቂም በቀል ተውልዶ ጎርምሶ፤
በጥፋት ዋሻ ደደቢትኛ፤ ድብትርና መልኩሶ፤
ጊዜ ሎቴሪ ሲያወጣለት የወረረን ገስግሶ፤
ቀኑ ሲመሽ 'መላዕክ ነኝ' ይለናል ዛሬደርሶ።

በጊዜ ጎደሎ ቅራቅንቦውን አግበስብሶ፤
መተት ቋጥሮ የሰይጣን ባህታዊ ኮሦሶ፤
በአህያ ጭኖ ስኳር በሶ፤
መርዝ የጋተን ማር አልሶ፤
በመረጋጋት አለሳልሶ፤
ሽፍታው ሲያከትምብን ኮንሶ፤
ቤተ መንግሥት አጉራ ጥሶ፤
በምንይልክ እልፍኝ ነግሶ፤
አርስ አይድለም እንዴ? አገር ያሳጣን አፈራርሶ።

ማን ሆነና ዛሬ መልሶ፤
ደረቅ ዘንባባ ልጥ አርሶ፤
ቄጠማ ጉዝጓዝ ነስንሶ፤
እሚማጠነን ተለሳልሶ፤
እንዳልገረፈን ተመላልሶ፤
ዘር ጅራፍን ደም ለውሶ፤
ከመቼ ወዲህ ለሕዝብ፤ለሀገር ደግሶ፤
አዛኝ ቂቤ አንጋች ውስዋሶ፤
ጥፍት ሴራ እንጂ የጭቃ እሾህ ተላብሶ፤

ቆርጦ ቀጣይ እምነት ማተብ በጥሶ፤
ጣና ባለስን እንዳልነበረ አፈራርሶ፤

መንጋ በጥባጭ የጠራውን አደፍርሶ፤
በአባይ ግድብ ጠብ ጠንስሶ፤
ሊሸነግለን አድበስብሶ፤
ጆሚራው የእርግብ ላብ ኮፍሶ፤
የማይታይ የማይጨበት ሙት ራዕይ ጸንሶ፤
ስናንጋጥጥ የሚቀብረን በቁማችን አንጋዳ ምሶ፤
እየገፋን ወደ ገደል ሳር አልብሶ፤

የመከራ ቸነፈር አውርሶ፤
በዘር ቋንቋ አናክሶ፤
ትውልድ  አሜርሶ፤
እምነት፤ሃውልት ሕግ ጥሶ፤
የጥፋት ቁርሾ ለኩሶ፤
ይኸ ሁሉ የ20 ዓመት ሰቆቃው አንሶ፤
ዛሬ ደግሞ ጦር ደግሷል ሊያጠፋፋን ጨርሶ።

አነሆ አሁን ቅዥቴ፤ኢትዮጵያዊያን የጋራ ቅዠታችን ሌሊት የአልጋ ጥግ ይዘን ሳይሆን፤በጠራራው ጸሃይ በቀን ጎደሎ በቁም እያየን፤በእንብርክክ እየዳህን ነው።

እስኪ ይህ ቀን መሽቶ፤ነግቶ ሌላ ህልም፤ ደግ ሕልም እንድናይ፤ ሳንተኛ አሁኑኑ በእውን እናልም!፤አልመንም በእውን እንፍታ።

ቸር እናልም! ቸር ይግጠመን!

የጐንቻው!            yegonchaw@yahoo.co.uk            June, 2013